# የፌዴራል መከላከያ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን
# ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

የፌዴራል መከላከያ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መመሪያው እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መከላከያ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ማሻሻያ

የፌዴራል መከላከያ የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

፩. አንቀጽ ፯(፪) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ ፪ ተተክቷል፡፡

> "፪. በመከላከያ ሠራዊት ፋውንዴሽን በኩል ሊቀርቡ የሚችሉ የተለያዩ የቀለብ ዓይነቶች፣ ወታደራዊ ዩኒፎርሞች፣ የሰርቪስ ተሽከርካሪዎች ኪራይ እና የመሳሰሉት የዕቃዎችና የአገልግሎቶች ግዥ በቀጥታ ከፋውንዴሽኑ መፈፀም ይቻላል"

፪. ከአንቀጽ ፯(፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡፡

> "፫. ሚኒስቴሩ የሚያከናውናቸውን ሚስጥራዊ ይዘት ያላቸውን ህትመቶች ግዥ ከብራና ማተሚያ ድርጅት በቀጥታ መፈፀም ይችላል፡፡"

፫. የአንቀጽ ፯(፫) አንቀጽ ፯(፬) ሆኖ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

> "፬. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩-፫ መሠረት ግዥዎች መፈፀም የማይቻል ሆኖ ከተገኘ በሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሠራተኛ በሚሰጥ ውሳኔ መሠረት ግዥውን ያለ ገንዘብ ጣሪያ እንደሁኔታው በውስን ጨረታ ወይም ከአንድ አቅራቢ በቀጥታ ማከናወን ይቻላል፡፡"

## ፫. ማሻሻያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ማሻሻያ ከ_____ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ _____ቀን 2006 ዓ.ም**

**ሱፍያን አህመድ**
**የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር**